DV2008

እንዳትታለሉ !!

ስለ ዲቪ እውነቱን ይወቁ !!

የአሜሪካን ኤምባሲ ከዚህ የሚከተሉትን እንድታውቁ ይፈልጋል::

ማመልከቻ:- ማመልከት የምትችሉት ከዚህ ጽሁፍ መጨረሻ የተመለከተውን ድረ ገጽ በመጠቀም ብቻ ነው:: ከአንድ ጊዜ በላይ አመልክተው ቢገኙ ማመልከቻዎ ወዲያውኑ ይሰረዝብዎታል:: ***አንድ ጊዜ ብቻ ያመልክቱ::***

የማመልከቻው ይዘትና ፎቶግራፍ :- ለማመልከቻዎ ኃላፊነቱን የሚወስዱት እርስዎና እርስዎ ብቻ ነዎት:: በሚያመለክቱበት ጊዜ ፎቶ ግራፍዎንና የሞሉት ቅጽ ትክክል ካልሆነ ማመልከቻዎ ተቀባይነት አይኖረውም:: ማመልከቻዎን ከመላክዎ በፊት በቅጹ ላይ የሰፈረው መረጃና ፎቶ ግራፍ የርስዎ መሆኑን ያረጋግጡ::

መመረጥ:- ሁሉም የዲቪ ሎተሪ አሸናፊዎች ቪዛ ያገኛሉ ማለት አይደለም:: ለዲቪ አሸናፊነትዎን የሚያስረዳ መልዕክት ሲደርስዎ ሂደቱን ለመቀጠል ከአሜሪካን መንግሥት ተጨማሪ ቀነ ቀጠሮን የሚገልጽ ደብዳቤ ሊደርስዎት ይገባል:: ቪዛ ሳያገኙ ምንም አይነት የጉዞ እቅድ አያውጡ::

ክፍያ:- ለዲቪ ሎተሪ ለማመልከት ምንም ዓይነት ክፍያ የለውም:: የማመልከቻዎን ቅጽ ለመሙላት ጉዳይ አስፈፃሚም ሆነ ተወካይ አያስፈልግዎትም:: አሸናፊዎች የዲቪ ክፍያ መክፈል ያለባቸው ጉዳያቸው መታየት ሲጀምር ለአሜሪካን ኤሜባሲ ብቻ እንጂ ለሌላ አካል መሆን የለበትም::

ስፖንሰር:- **ለዲቪ ብቁ ለመሆን ምንም አይነት ስፖንሰር አያስፈልግዎትም::**

ጋብቻ:- ለዲቪ ብቁ ለመሆን ሲባል ማግባት አያስፈልግዎትም:: ለምንም ዓይነት ምክንያት ብለው **ህጋዊ ያልሆነ** ጋብቻ መመስረት የለብዎትም:: ትክክለኛ ያልሆነ ጋብቻ በቀሪው የህይወት ዘመንዎ ወደ አሜሪካን አገር ለመሄድ ብቁ እንዳይሆኑ ሊያደርግ የሚችል እገዳ ይጥልቦታል::

ቤተሰብ:- ባለቤትዎንና ዕድሜአቸው ከሃያ አንድ ዓመት በታች የሆኑ ልጆችዎ ሁሉ ለዲቪ በሚያመለክቱበት ወቅት በቅጹ ላይ መሞላት አለባቸው:: ከላይ የተጠቀሱትን የቤተሰብዎን አባላት ስም በሙሉ መመዝገብዎን እንዳይረሱ መጠንቀቅ ይኖርብዎታል::

ትምህርት:- ለዲቪ ብቁ ለመሆን ከሚከተሉት ውስጥ አንዱን የግዴታ ማሟላት ይገባዎታል::

- የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ መልቀቂያ ፈተና በአምስት የትምህርት ዓይነት የማለፊያ ውጤት /ከA እስከ D/ ወይም በአምስት የትምህርት ዓይነት ከ20 ነጥብ በላይ
- 10ኛ ክፍል ማጠናቀቅና በተጨማሪ ሁለት ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሙያ ስልጠና ማስረጃ /10 +2 /
- ከኢትዮጵያ ከፍተኛ ወታደራዊ ትምህርት ተቋም የተመረቀ

ተፈላጊው የትምህርት ደረጃ ወይም ተመጣጣኝ የሁለት ዓመት የሥራ ልምድ ከሌለዎት ለዲቪ አያመልክቱ

ኢ-ሜል:- የአሜሪካን መንግስት የዲቪ አሸናፊ መሆንዎን ለመግለፅ በፍጹም በኢ-ሜል አይጠቀምም:: የአሸናፊነትዎን መልዕክት ሊቀበሉ የሚችሉት በፖስታ ብቻ ነው:: የዲቪ አሸናፊ ሆነዋል የሚሉ ኢሜሎች በሙሉ ማታለያዎች ናቸው::

ማስረጃዎች:- የሐሰት ማስረጃዎችን ለአሜሪካን ኤምባሲ ማቅረብ የለብዎትም:: ካቀረቡ ግን በትክክል ይደረስብዎታል:: የሐሰት ማስረጃዎችን ካቀረቡ በቀሪው ዘመንዎ በሙሉ አሜሪካን አገር ከመሄድ ይታገዳሉ::

ዲቪ 2008 ምዝገባ ከመስከረም 24 ቀን 1999 እስከ ህዳር 24 ቀን 1999 ድረስ ክፍት ይሆናል:: ያለምንም የማመልከቻ ክፍያ በሚከተለው ድረ ገጽ መመዝገብ ይችላሉ:: http://www.dvlottery.state.gov

ይህ በራሪ ወረቀት በአሜሪካን ኤምባሲ በነፃ የሚታደል ነው::